# ግንቦት 7 እና የአማራ ገበሬ ላይ የሚሰራው ሸፍጥ (ጌታቸው ሺፈራው)

September 12, 2018



አርበኞች ግንቦት 7 እንደ ድርጅት ድክመትም ጥንካሬም ይኖረዋል። ከእነ ድክመቱ ስናወሳቸው የነበሩ ጥንካሬዎችም ነበሩት። ለሀገርና ለድርጅቱ ሲባል ተሸክመናቸው የቆየናቸው ድክመቶች አሉ። የሚያውቋቸው ያውቋቸዋል። በቅርቡ ብዙ ትችቶችን ያስተናገደው፣ እኔም በግልፅ ለመተቸት የተገደድኩበት በገበሬው ላይ የሚሰራውን ሸፍጥ ነው።

አርበኞች ግንቦት 7 ኤርትራ ውስጥ ብዙ ሰራዊት እንዳለው ሲገልፅ ቆይቷል። በቅርቡ የአርበኞች ግንቦት 7 ካምፖች ፈርሰው ወደ ሀገር ቤት የገቡት ከ300 የሚበልጡ አይመስለኝም። በሁመራ በኩል የገቡት ከ300 ያነሱ ናቸው። ኤርትራ የሚገኘው ሰራዊት ቁጥር ይፋ እንደሚወጣ ያወቀው ድርጅቱ ፕሮፖጋንዳውን ማስተካከል የፈለገው ሀገር ውስጥ 5 ሺህ ጦር አለኝ በማለት ነው። ይህን የተናገረው እውቁ አንዳርጋቸው ፅጌ ነው። ሀገር ቤት አለ ለተባለው ሰራዊት አርበኞች ግንቦት 7 በአንድ ወቅት እገዛ ሲያደርግለት ነበር ከተባለው አረጋ ባሻገር በየ አካባቢ ያለውን የአማራ ገበሬ ነው የተማመኑት። የዚህ ፕሮፖጋንዳ አደጋው በግሉ በሬውን ሸጦ መሳርያ የገዛውን የአማራ ገበሬ የሚያስወርስ መሆኑ ነው። ግንቦት 7 የገንዘብ አቅም፣ የሚዲያ ተደራሽነትና ልምድ ያላቸው ፖለቲከኞች ያለው ድርጅት ነው።

ያለፈው አልፎ እንደ አዲስ ድርጅት፣ ባለው ቢቀጥል እንኳ ብዙ መወዳደር ይችል ነበር። የሆነው ግን ከዚህ በተለየ ነው። የአማራ ገበሬዎችን አለኝ ያለው ጦር ማሟያ ማድረግ ነው የፈለገው።

አርበኞች ግንቦት 7ወደ ሀገር ቤት ለመግባት መግለጫ በሰጠበት ወቅት አንድ ነገር ግልፅ አድርጓል። ከሰላማዊ ትግል ውጭ እንደማይደግፍ ብዙዎች የታዘቡትን መግለጫ አውጥቷል። እነ ዶክተር አብይ አህመድ ስለ ታጣቂ ቡድኖች ግልፅ አድርገዋል። ጦራቸው ትጥቅ እንደሚፈታ መግለጫ ሰጥተዋል። ኤርትራ የነበረው የአርበኞች ግንቦት 7 እና የአዴኃን ሰራዊት ትጥቅ ፈትቶ ገብቷል። ሀገር ውስጥ አለ የተባለ እና ለሀገር ውጭ የነበረው ሰራዊት የሚለየው በነበረበት ቦታ ብቻ ነው። ሰራዊት ትጥቁን ይፈታል ከተባለ ሀገር ውስጥ አለን ያሉትም እንዲፈታ ይገደዳል።

አርበኞች ግንቦት 7 በተለየ አካባቢ መልማልይም፣ አባልም ሊኖራቸው ይችላል። ገበሬዎቹ ግን አጉል ተስፋ እየተሰጣቸው በሀሰት አባል ተብለው እንደሚመዘገቡ ይገልፃሉ። ለምሳሌ ሲሳይ አንዱ ነው። ሲሳይ የአርበኛ ጎቤ መልኬ የሰራዊት አባል የነበረ ነው። የአርበኛ ጎቤ ጦር ሲበተን እነ ሲሳይም የሚሰበስባቸው አላገኙም። ይህን ለአንድ በአርበኞች ግንቦት 7 ስም ተከስሶ የነበረ የጎንደር ሰው ያናግረዋል። ይህ ሰው "በቃ ለግንቦት 7 ልመዝግባችሁ፣ አባል ነን በሉ" ይላቸዋል። የተበተኑት የጎቤ ልጆች የግንቦት 7 አባል ሳይሆኑ አባል ነን ብለው መመዝገባቸው ምን እንደሚፈይድላቸው ይጠይቁታል። "የተደበቀ መሳርያ ካላችሁ ተመዝግቦ ሕጋዊ ሆኖ እንድትይዙት እናደርጋለን" ይላቸዋል። መሳርያ እንደሌላቸው ሲነግሩት "ከአሁን በኋላ ብትገዙም ሕጋዊ እንዲሆን እናደርጋለን" ይላቸዋል። ለገበሬዎቹ ይህ አንድ ተስፋ ነው። መዝጋቢው ብርሃኑ፣ ደሞዜ፣ አለልኝ፣ ሲሳይና ሰጠኝ የተባሉትን ወጣቶች ይመዘግባል። መሳርያ አላቸው ብሎ ስለመዘገበ የሀሰት የመሳርያ ቁጥርም መዝገቡ ላይ አስፍሯል። ይህ መዝገብ ትናንት መስከረም 1/2011 ዓም "ለበላይ አካል ደርሶ መፍትሄ ታገኛላችሁ" ይላቸዋል። ለሌላ ሰው ሲያጫውቱት "ግንቦት 7 የመሳርያ ፈቃድ ለማሰጠት አይችልም፣ የሌላችሁን መሳርያ እና የሀሰት ቁጥር መመዝገቡም ተገቢ አይደለም" ብሎ ሲሳይን ወደእኔ ያመጣዋል። ሲሳይ በአማራነቱ ይታገል እንደነበር፣ የጎቤ ሰራዊት አባላትን የሚሰበስብ በመጥፋቱ፣ መሳርያም ከገዛ ሕጋዊ እንደሚሆን ስለተነገረው የሀሰት ቁጥር እንዳስሞላ አጫወተኝ።

ሲሳይ ያጫወተኝን መዝግቤ፣ የግንቦት 7 አባል ናችሁ ብሎ ወደመዘገባቸው ወዳጄ ደወልኩ። መዝጋቢወወ ሲሳይ ያጫወተኝን አልካደም። ከመታሰሩ በፊት በአማራነቱ መታገሉን አሁንም የግንቦት 7 የአቀባበል ኮሚቴ አባል እንጅ የግንቦት 7 አባል እንዳልሆነ ገለፀልኝ። ወጣቱ ጎንደር ሕብረትንም እንደተቀበለ አውቃለሁ። የግንቦት 7 አቀባበል ኮሚቴ መሆኑን አምኗል። የአቀባበል ኮሚቴ አባል ሆኖ ለምን አባል ብሎ እንደሚመለምል ላነሳሁለት ጥያቄ አጥጋቢ መልስ አልሰጠኝም። የመዘገባቸው እነሱን ለማገዝ ከመሆኑ ውጭ ለምን መሳርያ ሳይኖራቸው መሳርያ አላቸው ብሎ እንደሚመዘገብም ለጠየኩትም አጥጋቢ መልስ አልነበረውም። ግንቦት 7 የትጥቅ ትግል እንደማይደግፍ፣ እነዚህ ገበሬዎች ነገ ህጋዊ ይሆንልናል የሚሉት መሳርያ ሊቀማ እንደሚችል፣ ይህ ስልት የአማራ ገበሬን መሳርያ

ለማስወረድ እንደስልት ሊሆን አይችልም ወይ? ብየ ሳነሳለት ወጣቱ "ሰላማዊ ትግሉ ካላዋጣስ? አውርድ ቢልስ ማን ያወርድለታል?" ከማለት ውጭ አጥጋቢ መልስ ሊሰጠኝ አልቻለም።

የጎቤ ጦር አባል የነበረውንና የግንቦት 7 አባል ተብሎ ከተመዘገበ በኋላ "ተሳስቼ ተመዝግቤያለሁ!" ያለው ሲሳይ ጋር እያወራሁ አንድ አዲስ አበባ የሚገኝ ወዳጄ ይደውልልኛል። ይህ ወዳጄ የግንቦት 7 አባል ቢሆንም ትችት አቀረብክ ብለው እንዳኮረፉኝ የድሮ ወዳጆቼ አይደለም። ዛሬም የደወለው "ግንቦት 7ን መተቸትህ አይከፋም። ባህርዳር ላይ አትምጡ ሲሉን ለምን አትመክራቸውም" ብሎ ቀና ትችት ሊየቀርብ ነው። ይህን ስሰማ አንድ ሰው መኖሩም ደስ ብሎኛል።

ይህ ሁሉ ጥላቻ የመጣው በድርጅቱ ስም በሕዝብ ላይ በሚሰራው ያልተገባ ስራ መሆኑን ከጎኔ ቁጭ ብሎ የነበረውን ሲሳይን ጉዳይ ጠቅሼ በአማራ ገበሬ ላይ የሚሰራውን ሸፍጥ፣ የመዝጋቢውን ስም ጠቅሼ ድርጅቱ ይህን የመሰለ ሸፍጥ ሲሰራ ዝም የሚለው ሀገር ውስጥ አለኝ ብሎ ያስነገርን ጦር ቁጥር ለመሞላት ሲል የአማራ ገበሬን መሳርያ ለማስወረድ የገዥዎቹ መሳርያ እየሆነ እንደሚገኝ አጫወትኩት። ይህ ወዳጄ በድርጅቱ ስም ያልተገቡ ነገሮች ሊሰሩ እንደሚችሉ አጫወተኝ። ይህን ግን አንድ ቀን ድርጅቱ ተቃውሞ አያውቅም። እንዲያው ወዳጄ ግንቦት 7 እና አብይ አህመድ መግለጫ የሰጡበትን ጉዳይ ተቃርኖ የሚመዘገቡት ገበሬዎች መሳርያ የማያወርዱበትን ምክንያት ተከራከረኝ።

ቁም ነገሩ፣ እነ አንዳርጋቸው በሰጡት መግለጫ የጠሩትን የጦር ቁጥር ለማሟያነት የአማራ ገበሬ "መሳርያህን ህጋዊ እንደርግልሃለን" እየተባለ እየተመዘገበ ነው። የተገባለት ቃል ትክክል አለመሆኑንና መሸወዱን ሲያውቅ ደግሞ በቪዲዮም መግለጫ ሰጥቷል። እንደ ሲሳይ በስህተት መመዝገቡን እየተናገረ ነው። የግንቦት 7 አባል አይደለሁም፣ ግን መዝግቤያቸዋለሁ ያለው ወጣት እንዳመነውም ብዙ ገበሬዎች ቃል እየተገባላቸው እንዲመዘገቡ እየተደረገ ነው። የአዲስ አበባው ወዳጄ ጋር እንደተማመንነውም በድርጅቱ ስም መሰል ሸፍጦች እየተሰሩ ነው።

ነገር ግን እስካሁን ገበሬዎቹ የግንቦት 7 አባል ናቸው ተብለው ሲመዘገቡ፣ እና ትችት ሲቀርብ ድርጅቱ በስህተት ነው አላለም። ግንቦት 7 መሳርያን ህጋዊ የማድረግ አቅምና መብት ሳይኖረው ሕጋዊ እናደርግላችኋለን እያሉ ተታልለው እንደሚመዘግቡ ስንናገር፣ ስንፅፍ የአባላቱ የስድብ ውርጅብኝ እንጅ የድርጅቱ ማስተካከያ ተሰምቶ አይታወቅም።

ግንቦት 7 ከሰላማዊ ትግል ውጭ እንደማይንቀሳቀስ ተናግሯል። በሀገር ቤት አሉ የተባሉት አባሎቹ በካምፕ እንደሚቆዩ ተነግሯል። ሕጋዊ ያልሆነ መሳርያችሁ ይመዘገባል፣ ቀድሞ የተቀማችሁት ይመለስላችኋል እያሉ የ5 ሺህ ኮታን ለመሙላት የሚጥሩት መዝጋቢዎች ከድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ባይግባቡ ኖሮ እስካሁን ማስተካከያ ባይሰጥ እንኳ ተግባሩ በቆመ ነበር። ባለፈው በፎቶ ሲወጣ የሚያመጣውን ችግር ስለታየ ዛሬ ፎቷቸው ሳይወጣ በመዝገብ ብቻ ቁጥሩን ለመሙላት እየተሯሯጡ ነው። ግንቦት 7 ኤርትራ ውስጥ አለኝ ያለው ጦር በተባለው መጠን አልተገኘም። ይህን ለማስተካከል

ኮታውን የጣለው በአማራው ገበሬ ላይ ነው። የአማራ ገበሬ ስስ ብልት መሳርያው ነው። የተነጠቅከው መሳርያህ ይመለስልሃል፣ የድብቅ መሳርያህ ይመዘገብልሃል፣ ስትገዛ ህጋዊ ይሆንልሃል እየተባለ ማሚያ እየሆነ ነው። በየአካባቢው ባሉ መዝጋቢዎች በሀሰት የሚመዘገበው ገበሬ ነገ መሳርያውን አውርድ መባሉ የማይቀር ነው፣ መሳርያ ሳይኖረው የተዘመገበው ደግሞ መሳርያህን አምጣ እየተባለ ሊከላተም ነው።

ግንቦት 7 በአንድ ወቅት ያደረገው የተሳሳተ ቅስቀሳ ካለ ስህተት ነበር ብሎ ወይ እንዲሁ ማለፍ እንጅ በአማራ ገበሬ ላይ ተረማምዶ ስህተቱን ሊያስተባብል አይገባም። መልማይና መዝጋቢዎቹ ስህተት ከሰሩም አቁሙ ሊባሉ ይገባል። በእርግጥ እነ አንዳርጋቸው የሰጡትን መግለጫ የተመለከተ የአማራ ገበሬ በድርጅቱ ውሳኔ የድርጅቱን ስህተት መሸፈኛ እንዲሆን ስምምነት ሳይደረስ እንዳልቀረ ይረዳል። ግንቦት 7 በ5 ሺህ የአማራ ገበሬ እጣ ላይ ተረማምዶ ስህተቱን ሊሸፍን ዝም ማለት አይገባም። ይህ በመጀመርያ ከአባላቱና ደጋፊዎቹ የሚጠበቅ ነው። ድርጅቱ እና አባላቱ ይህ የለየለት የፖለቲካ ንግድ እንዲቆም ቢያደርጉ የሚጠቅማቸው ለራሳቸው ነው። ይህ ሸፍጥ የማይቆም ከሆነ ለአማራ ሕዝብ ቆመናል የሚል አካል ሁሉ በቀላሉ አይቶት ሊያልፍ አይገባም። ለአማ ሕዝብ ቆሜያለሁ እያለ በአማራ ገበሬ ላይ ሲነገድ ካልቆመለት ለማን ሊታገል ነው?